# የኢትዮጵያ የሕብረተስብ ጤና ኢንስቲትዩት እለታዊ ኖቬል ኮሮና ቫይረስ አስመልክቶ የሚወጣው ዕለታዊ መረጃ

## እለታዊ ዓለምአቀፍ መረጃ፡

- በዓለም የጤና ድርጅት ሪፖርት መሰረት እስከ ጥር 27/2012 ይህ መረጃ እስከ ተጠናቀረበት ሰዓት ድረስ ያለው በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች ቁጥር ሀያ አራት ሺህ አምስት መቶ ሀምሳ አራት (24,554) ሲሆን እስከ ጥር 26/2012 ድረስ አራት መቶ ሃያ ስድስት (426) ሰዎች በቫይረሱ ምክንያት ህይወታቸው ሊያልፍ ችሏል፡፡ ከቻይና ውጪ በፊሊፒንስ አንድ ሞት ተመዝግቧል፡፡

## እለታዊ የሀገራችን መረጃ

- በቦሌ አየር ማረፊያ በመንገደኞች ላይ በሚደረገው የሰውነት ሙቀትና የበሽታው ምልክቶች ልየታ እንዲሁም ከሕብረተሰቡ የሚሰጡ ጥቆማዎችን መሰረት በማድረግ በሁለት ሰአት ጊዜ ውስጥ የማጣራት ስራ እየተሰራ ነው፡፡
- ይህ መረጃ እስከ ተጠናቀረበት ሰዓት ድረስ ሶስት የበሽታውን ምልክት ያሳዩ ሰዎች በሽታው እንደሌለባቸው እስኪረጋገጥ ድረስ በለይቶ ማቆያ ማዕከል ውስጥ የህክምና ክትትል እየተደረገላቸው ይገኛል፤ ለተጨማሪ ምርመራ ናሙናዎችን ለመላክ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ተጠናቋል፡፡ በአሁኑ ስዓት የበታሸውን ምልክት ያሳዩና በለይቶ ማቆያ ማእከል ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ቁጥር አራት ነው፡፡
- ከዚህ በፊት ጥር 25/2012 ወደ ደቡብ አፍሪካ ለምርመራ ተልከው የነበረው የአራት ሰዎች ናሙናዎች ከቫይረሱ ነጻ ስለመሆናቸው ውጤቱ በዛሬው እለት የደረሰን ሲሆን የነበረው የጤና ክትትል ተቋርጧል፡፡
- ኖቭል ኮሮና ቫይረስ ወደ ሀገራችን እንዳገባና ቢገባም ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ስራዎችን ለማከናወን የጤና ባለሙያዎች በማሰልጠን፣ ባለሙያዎችን በለይቶ ማቆያ ማእከላትና በአለም አቀፍ በረራ በሚያስተናግዱ የአየር መንገዶች በመመደብ የበሽታ ቅኝት ስራዎች ተጠናክርው እየተከናወኑ ይኛሉ፡፡ ከዚህም ጋር በተያያዘ በማቆያ ማዕከል ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር ንክኪ ያላቸው ሰዎች የጤና ሁኔታ ባሉበት ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡
- ከቻይና የሚመጡ መንገደኞችን በስልክ የጤና ሁኔታቸውን ለመከታተል እንዲቻል ባለሙያዎች እና አስፈላጊውን የቴሌኮም ቁሳቁሶች ግዥ በመከናወን ላይ እንገኛለን፡፡
- ለሁሉም ክልሎች ከበሽታዉ ጋር በተያያዘ የጤና ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁሶች ድጋፍ ተደርጓል፡፡

## ጥንቃቄ መደረግ ያለባቸው ጉዳዮች

- ሕብረተሰቡ የኮሮና ቫይረስ ከገባባቸው ሀገራት የመጡ መንገደኞች እንዲሁም ከነዚህ ግለሰቦች ጋር ንክኪ የነበራቸው ሰዎች የበሽታው ምልክቶች (ትኩሳት፤ ሳል፤ የትንፋሽ መቆራረጥ፣ የመተንፈስ ችግር) ከታዩባቸው በአስቸኳይ በ8335 ነጻ የስልክ መስመር ላይ በመደወል ሪፖርት ያድርጉ፡፡
- የበሽታው ምልክት የታየባቸው ሰዎች በሚያስነጥሱበት እና በሚያስሉበት ወቅት አፍና አፍንጫን በሶፍት ወይም በክርን መሸፈን፤ የተጠቀሙበትን ሶፍት ማቃጠል እንዲሁም እጃቸውን በሳሙና በመታጠብ የቫይረሱን ስርጭት ይከላከሉ፡፡
- በተጨማሪም በሀገራችን እስካሁን በቫይረሱ መያዙ የተረጋገጠ ሰው አለመኖሩን አውቆ ሳይዘናጋ ህብረተሰቡ ጥንቃቄ ኢንዲያደርግ ኢንስቲትቱ ያሳስባል፡፡

ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

Ethiopian Public Health Institute

የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
አዲስ አበባ
27/6/2012 ዓ.ም